PANORAMA # XXXIII

## የትዝብት አድማስ

**ሐምሌ** 11 **ቀን** 2000 **ዓም**

## አይበገሬነት

***ህልም እንደፈቺ እንደሚባለው፥ አይበገሬነትን አስመልክቶ፥ ልዩ ልዩ ክፍሎች እንዳሻቸው ልዩ ልዩ ትርጉምና ፍች ሲሰጡት እንሰማለን:: አንዳንዶቹ፥ አይበገሬነትን፥ እንደ አክራሪነት፥ ፅንፈኝነት፥ ግትርነት፥ ወዘተ ሲቆጥሩት፥ ሌሎች ደግሞ፥ እንደ ሞኝነት፥ አላዋቂነት፥ እንዲያውም አልፈው-ተርፈው እንደኋላ-ቀርነት ያዩታል:: ሁሉም ሲጠቃለሉ ግን አይበገሬነትን ጥላሸት ለመቀባት የሚያስገድዳቸው የጋራ ግንባር ይፈጥራሉ:: ሁሉም ሄደው ሄደው የሚገናኙበት የጋራ ግብ አላቸው:: ጊዜው እየመሸብን ነዋና እንደምንም ብለን ከትግሉ ተገላግለን፥ ያለውን ሥርዓት እየጠጋገንን እናገልግል ከሚል የጋራ የተንበርካኪነት ድምዳሜ ይደርሳሉ:: በመሆኑም፥ አይበገሬነትን እንደ ጦር የፈሩታል:: አይበገሬዎቹንም፥ እንደ አባታቸው ገዳይ ይጠሏቸዋል:: ፍርሃትና ጥላቻ ሲተባበሩ ደግሞ፥ የቱን ያህል ጥፋት እንደሚያስከትሉ መገመት ከባድ አይሆንም:: እነኝህ የተንበርካኪ ዓላማን ለማራመድ የሚከጅሉ ሁሉ፥ አይበገሪዎቹን የሚያዩአቸው፥ እንደ ጉሮሮ አጥንት ነው:: አይበሉ አያስበሉ ዓይነት ነገር:: "መለኮን ስታረጅ፥ ደላላ ትሆናለች" እንደሚባለው፥ የትግል እርሿቸው የተሚጠጠባቸው ደግሞ፥ ወደ ተኀብዳጅነት ተዘዋውረው ወሬ አመላላሽ እንደሚሆኑ አያሌ ተመክሮዎች አስረድተዋል:: በየትኛውም ሥርዓተ ማኀበር ውስጥ፥ እስከመጨረሻው ድረስ ከተነሱበት ዓላማ፥ ከገቡበት ሕዝባዊ ቃል ኪዳን ንቅንቅ ሳይሉ፥ ትግሉን የሚገፉ አይበገሬዎች ነበሩ:: አሁንም አሉ:: ወደፊትም መኖራቸው አይቀርም:: ኀብረተሰብና ትግል እስከሚኖሩ ድረስም ይህ ክስተት ይቀጥላል::***

***አይበገሬነት፥ የአይበገሬዎች ልዩ ባኀርይና ምግባር ስለሆነ፥ የሁለቱ እስከ መጨረሻው ተዋኀዶ መዝለቅ፥ የተነሱበትን ዓላማ ለመፈፀም እጅና ጓንት ሆነው ይቆያሉ:: ይህ ደግሞ በዘመናት የታየ ሀቅ ነው:: አይበገሬዎች ባይኖሩ ኖሮ፥ ቅኝ ገዥዎች፥ ጨቋኝ ሥርዓቶች፥ የሰው ሀገር ወራሪዎች፥ አምባገነኖች፥ ወዘተ... ዘለዓለም እንደገዙ፥ እንደጨቆኑና እንደወረሩ በቀሩ ነበር:: በአይበገሬዎች፥ የዓላማ ጽናት፥ የትግል መግፋት፥ ከባድ መሥዋዕት፥ እልህ አስጨራሽ ትግልን መቀጠልና "ወይ ፍንክች" ባይነት፤ ቅኝ ገዥዎች ተባርረዋል:: አምባ ገነኖች ተወግደዋል:: ወራሪዎችም ተደምስሰዋል:: ሀገራችንን በዘመናት ሊወርሯት የመጡትን ቅኝ ገዥዎች፥ በዘመኑ የነበሩት ወላጆቻችን በአይበገሬነት ባይደመስሳቸው ኖሮ፥ ኢትዮጵያ ሀገራችን፥ የነፃነት ጮራ የሚል ስም ባላተረፈችም ነበር:: ለዚህም ነው፥ በአደዋ ጦርነት የነበሩ***

ባለቅኔዎች፥ “አባቶች ተወልደው ባያነሱ  ጋሻ፥ ግብሩ ዕንቁላል ነበር ይህን ጊዜ ሀበሻ ።” ብለው የተቀኙት። የአይበገሬነት ባኅርይ፥ የኢትዮጵያ የጥንት ጀግኖች መለያ የነበረ ቢሆንም፥ የስድሳ ስድስቱ አብዮተኛ ትውልድም፥ የእነርሱን ጋሻ አንግቦ ተዓምር መስራቱ የቅርብ ትዝታ ነበር። የነዚያን መስዋዕታዊ ጓዶቻቸውን አደራ ተረክበው  ትግሉን የቀጠሉት አይበገሬወቹ፥ አሁንም በወይ ፍንክች ባይነታቸው ላይ ለመደራደር ዝግጁ የማይሆኑትም ከዚህ መሠረታዊ ቃል ኪዳን በመነሳት ነው።  ይህ ባኅሪያቸው፥ እንደ ግትርነት፥ አክራሪነትና ጽንፈኝነት ከተቆጠረባቸው፥ በፀጋ ከመቀበል አልፎ፥ ከማንም ጋር አፍ መካፈትን አይመርጡም።

አንድ አንድ ክፍሎች፥ አይበገሬነትን፥ የዲፕሎማሲ ዕውቀት የጎደለው ባዶ ግትርነት  ነው ብለው ራሳቸውን በማጽናናት፥ ባዶ እጃቸውን  ብቻ ይዘው ወደ ተጎብዳጅነት ጠረጴዛ ሲሯሯጡ እናያለን። ምናልባት ስለ ዲፕሎማሲ የተሸዋረረ ዕይታ ሊኖራቸው የ  ሉት፥ የጥንቶቹን ኢትዮጵያውያን የተራቀቀ ዲፕሎማሲያዊ ችሎታ ባለመገንዘባቸው ነው ብለን እንገምታለን።  የሀብተ ጊዮርጊስ አባ መላን የዲፕሎማሲ ችሎታን እንዲያስታውሱ ከመጋበዝ በቀር፥ በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ለማለት አንሻም። የሀገራቸውን ታሪክ ለመገንዘብ ካልፈለጉ ደግሞ። በዲፕሎማሲ ዕውቀቱ በዘመኑ ታላቅ ዝናን ያተረፈውን፥ በ19ኛው ምዕተ ዓመት የኦስትርያ መሪ የነበረውን የ  ንስለር መተርኒችን ታሪክ እንዲያነብቡ እንጋብዛቸዋለን። መተርኒች፥ የዲፕሎማቲክ ውይይትን አስመልክቶ እንዲህ ሲል ተናግሮ ነበር ይባላል። እንጠቅሳለን - “ ለዲፕሎማሲ ድርድር ወደ ጠረጴዛ  ስትቀርብ ባዶ እጅህን አትሂድ” የጥቅሱ መጨረሻ። ይህ አባባል ብዙ ትንታኔ የሚያስፈልገው አይመስለንም፥ ብልህ ለሆነ ሰው ማለታችን ነው። ለድርድር ከምትወያየው ክፍል ጋር ስትነጋገር፥ ይህን ካላመጣህ (ካልሰጠኸኝ)፥ እኔም ይህን አላመጣም(አልሰጥኽም) መባል መቻል አለበት። ባዶ እጅ ተይዞ የሚደረገው ድርድር፥ የሌላው (የተፃራሪው) ወገን በጎ ፈቃድንና ችሮታን ዓይን ዓይን ከማየት በስተቀር፥ ሊያመጣው የሚችል ምንም ፋይዳ እንደሌለው፥ ብዙ የታሪክ ማስረጃዎችን መጥቀስ ይቻላል።  በተፃራሪው ወገን ችሮታ የሚገኝ ማንኛውም የድርድር ስምምነት ደግሞ፥ ስትራተጂያዊ ዓላማን መሸራረፍ እንጅ፥ የሚያመጣው አስከባሪ ውጤት የለም።

“ቢሰበር አጥንቴ፥ ቢንቆረቆር ደሜ፥  
እኔ አልበገርም እስከ ትግል ፍጻሜ  
ያም ከዳ ያም ሄደ ብየ ለምን መጨነቄ፥  
እሰዋለሁ እንጅ ቃልኪዳን ጠብቄ  
ታሪክ ሳላበላሽ እስከ ዝ  ት ዓለሜ  
ይታገሏል እነጅ እስከ  ምልዓተ-ዕድሜ  
ለሕዝብ ነፃነት ለሀገር ልምላሜ”

ተብሎ የተዘመረውም፥ እንዲሁ ለይስሙላና ለመፈክር ማሰማት ብቻ ተብሎ አይደለም።  ከወያኔ ጋር የሚደረገው ማንኛውም ድርድር፥ ይዞት የሚቀርበው አንድ አስገዳጅ ኃይል ሊኖረው ይገባል። ያ ኃይል ደግሞ በአሁኑ ወቅት፥ መሳሪያ ያነገበ ሠረዊት፥ ወይም መድፍና ታንክ የሚያንከባልል ተዋጊ ኃይል

ሊሆን ባይችልም፥ ሁኔታው የማይለወጥበት ምክንያት ግን አይኖርም። አይበገሬዎቹ፥ ከተዋጊ ሠራዊት የበለጠ፥ ከመድፍና መትረየስ የላቀ ኃይል እንዳላቸው ማሳየት ይገባቸዋል። ይኸ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ኃይል ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድጋፍና ትብብር እንደሆነ መታወቅ አለበት። የመላውን ኢትዮጵያ ሕዝብ ትብብርና ተሳትፎ በጀርባው ያሰለፈ ማንኛውም ድርጅት፥ የትኛውንም ኃይል ወደ ጠረጴዛ ለድርድር ተገድዶ እንዲመጣ የሚያስችል ጉልበት እንዳለው የታወቀ ነው። ይህ እንዲሆን መታገል ደግሞ ግትርነት ሳይሆን፥ አየበገሬነት ነው። የዲፕሎማሲ ብልጠት ሳይሆን፥ የዓላማ ፅናት ነው። ኃያሉን የኢትዮጵያን ሕዝብ በጎኑ እንዲሰለፍ አድርጎ መታገል ፥ አክራሪነት ሳይሆን፥ ለኢትዮጵያ ስትራተጂያዊ ጥቅም፥ ግንባርን ሳያጥፉ መታገል ማለት ነው። የደቡብ አፍሪካን ዘረኛ ሥርዓት የደመሰሰው የነ ማንዴላ አይበገሬነት የዘመናችን የጽናትና የመሥዋዕት ተምሳሌት ነው። "ወንዶች ከሆናችሁ ኑና ሞክሩኝ፥ ይዋጣልን" ለሚሉ ባተሌ የወያኔ መሪዎች፥ ምላሹ ከእነርሱ ጋር እንካ ሰላንትያ ሳይሆን፤ የሚከተሉትን የትግል ስልቶች ነድፎ በቅደም ተከተላቸው ማስኬድ ብቻ ይሆናል።

1ኛ) ተወደደም ተጠላ፥ አሁንም አሁንም፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ በኩል ተደጋግሞ የሚጠየቀውና እስካሁንም ተፈላጊውን ምላሽ ያላገኘው፥ ወያኔን እንደ ኢትዮጵያ ስትራተጂያዊ ጠላት ፈርጆ ዘረኛ አገዛዙ በመደምሰስ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማስፈንን ነው። ይህ ጉዳይ አሁንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ስትራተጂያዊ ጥያቄ ነው። በመሆኑም በአስቸኳይ ስታራተጂያዊ መልስ ይጠብቃል።

2ኛ) የኢትዮጵያን ሕዝብ ከፅንፍ አስከ አጽናፍ ለትግል ማሰለፍ ወቅታዊ ብቻ ሳይሆን፥ አንገብጋቢ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። የኢትዮጵያን ሕዝብ ሁለንተናዊ ተሳትፎና ሚና ያገናዘበ ትግል፥ የቱን ያህል ስትራተጂያዊ ለውጥ እንደሚያስገኝ፥ ማመን አስፈላጊ ነው። ያልተቋረጠ ሕዝባዊ አመፅ፥ ማንኛውንም አምባገነን ሥርዓት እንደሚያንበረክክ፥ የስድሳ ስድስቱን የካቲት ብሔራዊ ሕዝባዊ ቁጣ ማስታወሱ ብቻ ይበቃል። ይህ እንዳይከሰት የወያኔ መሪዎች ሽንጣቸውን ገትረው እንደሚሠሩ በቅድሚያ መረዳት ይገባል።

3ኛ) በተቃዋሚ ድርጅቶች መካከል የሚደረገው የቀጥታም ሆነ የተዘዋዋሪ የቃላት ጦርነት በአስቸኳይ ሊቆም ይገባል። ጦርነቱ፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ያስከፋዋል እንጅ፥ የሚያስደስተው አይሆንም። የወያኔን መሪዎች ግን፥ እንደሚያስፈነድቃቸው የታወቀ ነው። በኢንተርኔትም ሆነ በተመሳሳይ የዜና ማሰራጫዎች የሚደረጉት ፀረ-አንድነት ፕሮፓጋንዳዎች ኢትዮጵያን የሚጎዳ እንጅ፥ የሚጠቅም አለመሆኑ ታውቆ ሊወገዝ ይገባዋል። ሁሉም ሰው ማዕቀብ ሊያደርግበት ግድነት ነው። በወያኔ መወገድ የማያወላውል አቋም ያላቸው ተቃዋሚ ድርጅቶች ቆራጥ እርምጃ ሊያስወስድ የሚያስችላቸውን ኃይል ካሰባሰቡ፥ የወያኔ ቅጥረኞች ቅስማቸው እንደሚሰበር የተወቀ ነው። መሃል-

ሰፋሪው ደግሞ የኃይል ሚዛኑን እያየ ሚናውን እንደሚለይ የትግል ተመክሮ ያስረዳል፡፡

4ኛ) ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ከወያኔ መንጋጋ ለማላቀቅ በሚካሄደው ትግል ያመረቃ ውጤት ማስመዝገብ የሚቻለው በተባበረ ክንድ ብቻ እንጅ በተናጠል እንዳልሆነ የሚያከረክር ባይሆንም፥ የዓላማ አንድነትና ጥንካሬ ከሌለ ግን የሰመረ ትግል ማድረግ ከቶ የሚቻል አይደለም፡፡ ይህም በመሆኑ ኅብረት ኅብረት ቢሉት ፋይዳ አይኖረውም፡፡ የተፍረከረከ ስብስብ እየጠፈጠፉ፥ ስትራተጂያዊ ትግል ማድረግ የሚቻልም አይሆንም፡፡ ይህንን ሀቅ በሚገባ ሳይረዱ እንዲያው በችንፌትና በመንበርከክ አይበገሬዎቹን፥ የተለያየ ስም በመለጠፍ፥ ከወያኔ ጋር በተናጠል ለመደራደር መሞከር፥ የታሪክን ትዝብትና የትውለድን ውግዘት ከማትረፍ በቀር፥ ለሀገር የሚጠቅም አንዳችም ፋይዳ አይኖረውም፡፡ የአይበገሬነትን ምንነት ከአድዋ ጦርነት ውጤት የተገነዘበ ኢትዮጵያዊ ትውልድ፥ የሚኖረው ምርጫ አንድ ብቻ ነው - ይኸውም፥ በዓላማው ፀንቶ እስከ መጨረሻው ሕዝባዊ ድል ድረስ መታገል፡፡ የአድዋን ታሪክ በደንብ የተገነዘቡ የአፍሪካ ሀገሮች፥ ከቅኝ ግዛት ለመላቀቅ ካስቻሏቸው ባኅርያት መካከል፥ አይበገሬነታቸው ነበር፡፡ የፈረንሳይን ቅኝ ግዛት ለማስወገድ የበቁት የነአህመድ ቤንቤላ፥ የነፈራሀት አባስ አይበገሬነት ነበር፡፡ ይህ ከሆነ ዘንዳ፥ አይበገሬነት ለእኛ ኢትዮጵያውያን፥ እንደ ሸቀጥ ዕቃ ከውጭ የመጣ ሳይሆን፥ ታሪካችን፥ ባኅላችን፥ መስተጋብራችንና ባኅርያችን በመሆኑ፥ የሕዝባችንን የመጨረሻ ስትራተጂያዊ ጥቅም እስክናስከብር ድረስ፥ በአይበገሬነት ከመታገል በስተቀር ሌላ ምርጫ ሊኖረን አይችልም፡፡

በአርበኝነት ትግል፥ ለነፃነት የሚደረገው ተጋድሎና አምባገነኖችን ለማስወገድ የሚካሄደው የፖለቲካ ትግል፥ በመጨረሻ የተጠበቀውን ድል ሊያስመዘግብ የሚችለው፥ አይበገሬዎቹ ግንባራቸውን ሳያጥፉ፥ ዓላማቸውን ሳይረሱ፥ ለሕዝብና ለሀገራቸው የገቡትን ቃል ኪዳን ሳያረክሱና ኢትዮጵያዊ ብኩርናቸውን በጭብጥ ምስር ሳይለውጡ በቆራጥነት እስከ መጨረሻው ሲታገሉ ብቻ ነው፡፡ ይህንን ታሪክ የሚሰሩ ደግሞ፥ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ጥቅምና ደኅንነት ሲሉ አይከፍሉ መስዋዕት የሚከፍሉና ስትራተጂያዊ ራዕይ ያላቸው ምርጥ ዜጎች ብቻ ናቸው፡፡ እነኝህ ዜጎች ሀገራቸውን ከወደቀችበት ማጥ ለማውጣት በዓላማ አንድነት የተደራጁ ብቻ ሳይሆኑ፥ በዕምነታቸው እንከን የማይወጣላቸው አይበገሬ ታጋዮች ናቸው፡፡ የእኛም አይበገሬነት ከቀደምት አርበኞችና ሰማዕታት ጓዶቻችን የወረስነው ጀግንነት በመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ የዘር አገዛዝ ነፃ ወጥቶ የራሱ ገዥ ለመሆን ዴሞክራሲ ሥርዓት እስከተጎናፀፈ ድረስ ከጎኑ ሆነን እንታገላለን፡፡ ይህን ከማድርግ ደግሞ፥ የማንንም ፈቃድ የምንጠይቅ አይደለንም፡፡ በቃል ኪዳናችን ፀንተን ከመታገልም የሚያግደን ኃይል ይኖራል ብለን አናስብም፡፡ ይህንንም የፀና አቋማችንን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ያውቀዋል፡፡